

# 8 ሠዓታት በገነት

**በሪካርዶ ሲድ**

ጌታ እንዲህ ይላል “***እነዚህን መልዕክቶች በምድር ወደሚኖሩ ሕዝቦቼ የምልከው እኔ በሰማያዊ መንግሥት ስለምኖር ነው።***”

ራዕይ 4፡1

*ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የነበረው የመለከት ድምጽ፦ ወደ ላይ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር እነግርሀለሁ አለ።*

ራዕይ 5፡11-12

*አየሁም፥ በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምጽ ሰማሁ፤ ቁጥራቸውም አእላፋት ጊዜ እልፍ፥ ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር። በታላቅም ድምጽ፦ የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም፣ ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ።*

እባካችሁ፥ ቤተ ክርስቲያን (ምእመናን) በእኔ ህይወት የሆነውን ስሙ። በህልም ውስጥ፥ ጌታ በእኔ ህይወት መሥራት ጀመረ። በዛ ህልም፥ከቤቴ ወጥቼ ስሄድ ትዝ ይለኛል። በመንደራችን እየሄድኩ ሳለ የሆነ ሰው እጄን ይዞ ወደ ላይ ወደ ሰማይ አነሳኝ እናም በሚገርም ፍጥነት እየተጓዝሁና እግዚአብሔርንም አከብር (ከፍ ከፍ አደርግ) ነበር። በላዬ ታላቅ ብርሃን መጣና ከብርሃኑ ውስጥ እንዲህ የሚል ድምጽ ተናገረኝ “***ሪካርዶ፥ ሪካርዶ፥ ሥራህን አቁም፤ በአንተ ህይወትና በምድር ባለችው ቤተ ክረስቲያኔ የሆነ ነገር መሥራት እፈልጋለሁ።***” ይህን ቃል እንደሰማሁ፥ እየተርበተበተሁ ተወራጩሁና ከህልሜ ነቃሁ። ተነሳሁና ወደ እግዚአብሔር ማልቀስና መጠየቅ ጀመርኹ “*ምንድር ነው ይሄ፥ ጌታ ሆይ?*”

ይህ ድምጽ በጣም ጠንከር ብሎ ወደ እኔ መጣ። ለብዙ ቀናት እንደዚህ ሆነብኝ። ለመተኛት ጋደም አልሁኝና ይህንኑ ህልም በድጋሚ አየሁ እናም ጌታ ያንኑ መልዕክት ደገመልኝ። ከተደጋጋሚ ጊዜ በኋላ እየጮህኩ መንቃት ጀመርሁ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ድምጽ በየጊዜው ኃይሉ እየጨመረ ስለሚመጣ ነው። እየተርበተበትኩ ስነሳ እጮህለው እናም ቤተሰቦቼ ይጠይቁኛል “*ምንድር ነው ነገሩ?*” ስለ ህልሙ እነግራቸዋለሁ፥ እና እናቴ ጸልያልኝ እንዲህ አለችኝ “*ጌታ እየተናገረህ ከሆነ እራሱ ማስተዋልን ይሰጥሀል።*” ነግቶ ወደ ሥራ የምሄድበት ሠዓት እስኪድርስ ድረስ ሌሊቱን ሙሉ ስንጸልይ አደርን። ከዛም እናቴ እንድዘገጀኝና ወደ ሥራ እንድሄድ ነገረችኝ። እየተናገረኝ ያለው እርሱ እንደሆነና እንዳልሆነ

እንዲያረጋግጥልን ከጌታ ዘንድ ምልክትን ጠየቅን። ገላዬን ታጠብኩ፣ ተዘገጃጅቼ ወደ ሥራ ሄድኩ። በ"ቺሊ ላብራቶሪስ" እሠራ ነበር።

የእውነት ሥራዬን እወድ ነበር። ወደ ሥራ ስሄድ ከአውቶቡስ ተራ ይወስዱኛል። ከባስ እንደወረድሁ፥ የሆነ ሰው እነዲህ አለኝ "*እዚህ ምን ታደርጋለህ? ከዚህ በኋላ እዚህ ቦታ መሆን አይገባህም።*" በብዙ አጋጣሚዎች፥ ሌሎችም ይህንኑ ነገሩኝ። የሚገርመው ነገር ዳግም የተወለዱ አለመሆናቸው። (ከውኃና ከመንፈስ [የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 3]) ይህ እግዚአብሔር የሰጠኝ ምልክት ነው። ከምልክቱ በኋላ ሥራዬን ለማቆም ወደ አለቃዬ ለመሄድ ወሰንኩ። እንዲህ አልኩት "*ድርጅቱን የግድ መልቀቅ አለብኝ ምክንያቱም ሥራዬን እንዳቆም እግዚአብሔር አዝዞኛል።*" እግዚአብሔር ካዘዘ **የግድ** መታዘዝ ይኖርብናል። አለቃዬ ስለእኔ በመጨነቅ ጠየቀኝ "*እና ምን ልታደርግ ነው? እንደዚህ ዓይነት ጥሩ ሥራ የት ታገኛለህ?*" እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለብኝ ነገርሁት። ስለዚህ ሁለት ሺህ ሰዎች የተገኙበት ታላቅ አሸኛኘት አደረጉልኝ። ከዛ በኋላ፥ እቃዬን ሁሉ ሰብስቤ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። እያለቀስኩ እቤቴ ስደርስ፥ እናቴ ከፊት ለፊቱ በረንዳ ላይ ቆማ እየጠበቀችኝ ነበር። ጌታ በእነዚያ ሰዎች ህልሜን ስላረጋገጠልኝ ሥራዬን እንዳቆምኩ ነገርኳት። እርሷም እንዲህ አለችኝ "*ጌታ ከተናገረህ፥ በህይወትህ እርሱ እንደ ወደደ ያድርግ።*"




ወደ ቤት ገባንና እስኪመሽ ድረስ አወራን። ከዛም ዛሬ ማታ ጌታ በህልም ስለሚያናግረኝ መተኛት እንዳለብኝ ነገርኳት። በህልም የሚያናግረኝ መስሎኝ ነበር። ነገር ግን እርሱ ያሰበው በሌላ መንገድ ነበር። መኝታ ቤት ገብቼ ልብሴን ሳወላልቅ ክፍሉ መናወጥ ጀመረ። ከዛ መጮህ ጀመርኹ "*ሳንቲያጎ፥ ቺሊን እየመታት ያለው መሬት መንቀጥቀጥ ነው!*" መኝታ ቤቴን ለቅቄ ለመውጣት ሞከርኩ፥ ነገር ግን የሆነ የማላየው ሰው በበሩ በኩል እንዳልወጣ ይከለክለኝ ነበር። በክፍሉ አሻግሮ እናቴና ቤተሰቦቼ ይታዩኛል፥ እንዲረዱኝ ተማጸንኩ ነገር ግን ማንም የሚሰማኝ አልነበረም። አሁን ይህ የማይታየው አካል የጌታ መልአክ እንደሆነ አወቅሁ። ወደ ኋላ ተመለስኩና አልጋዬ ላይ ተጋድሜ ምን እየሆነ እንዳለ እንዲነግረኝ ወደ እግዚአብሔር ተማጸንኩ።

ከዛም በግልጽ የሚሰማ ድምጽ ተናገረኝ። መንፈስ ቅዱስ እጅግ ደስ በሚል ድምጽ እንዲህ ሲል ተናገረኝ "***ሪካርዶ፥ አሁን ሥራህን ለቅቀሀል፥ በየቀኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድክ ስለህይወትህና በምድር ስላሉቸው ቤተ ክርስቲያኔ በቀን ለሰባት ሠዓታት ያህል እንድትጸልይ እፈልጋለሁ።***" ጌታ ተናግሮ እንደጨረሰ ክፍሉ መናወጹን አቆመ። ከዛም እጄን ወደ በሩ ዘረጋሁና ከክፍሉ ተመልሼ መውጣት እንደምችል አረጋገጥሁ። ከዛም ወደ እናቴ እሮጥኩና "*የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ሰማሁት*" ብዬ ጮህኩ እንደገናም ከቤት ወጣሁና እንደዛው እያልኩ መጮህ ጀመርኩ። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር አሁን ድረስ ለሰዎች እንደሚናገር አያምኑም ነገር ግን እውነቱን ነው የምነግራችሁ፥ እስካሁን ለሰዎች ይናገራል! አብርሃምን ማናገር ከቻለ እኛንም የዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን (ክርስቲያኖች) ሊያናግረን ይችላል! ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ከካህኑ ጋር ተነጋገርንና መጸለይና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም እንድችል ቤተ ክርስቲያኑን በየቀኑ ከጠዋቱ 2፡00 ሠዓት እንዲከፈት ተስማማን። ሁል ጊዜ ጠዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን እሄድና ለአንድ ሠዓት፣ ለሁለት ሠዓት እጸልይና በሦስተኛው የምጸልየው ነገር አጣለሁ፥ ከዛም እግዚአብሔርን እጠይቀዋለሁ "*ጌታ ሆይ፥ ምን ልጸልይ? ገና አራት ሠዓት ይቀረኛል!*"

ከዛ ከመሬት በታች ከቤተ ክርስቲያኑ የኋላ በር ጀምሮ የሚያልጎመጉም ነገር ሰማሁ። ከዛ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑ እንደ ሰከረ ሰው ሲንገዳገድ ተሰማኝ። በዚህ መንገዳገድ ውስጥ፥ በፊት በህልሜ እንደነበረው

ያይደለ በተለየ ድምጽ ጌታ ሲናገረኝ ሰማሁት። በፊት የተናገረኝ ድምጽ በስልጣን ነበር፥ አሁን ግን በሐዘኔታ ድምጽ አናገረኝ። እንዲህ አለኝ፦ "***ሪካርዶ፥ ሪካርዶ ለቤተ ክርስቲያኔ ጸልይ! ቤተ ክርስቲያኔ ከእንግዲህ እንደ ቀድሞ አይደለችም!! በምድር ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያኔ ተቀይራለች። ቤተ ክርስቲያኔ እምነቷን አጥታለች። ቤተ ክርስቲያኔ በእኔ ወይም በእኔ መኖር አታምንም! ሀያው እንደሆንኩ ለቤተ ክርስቲያኔ ተናገር!! ለቤተ ክርስቲያኔ ማልድ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያኔ እየጸለየችና እየጾመች አይደለም!***" ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ መናወጹ አቆመ። ከዛ በኋላ በቀሪው አራት ሠዓት እያማለድሁና በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ወደ ላይና ወደታች እያልኩ ስለእግዚአብሔር ህዝብ መታደስ መለመን ጀመርኩ።

ሐሙስ እለት በሁለተኛው የማማለድ ቀን፥ መገጣጠሚያዎቼንና አጥንቶቼን ጽኑ ህመም ስለተሰማኝ ለመነሳት አልፈለግሁም። እናቴ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂጄ እንድጸልይ እየቀሰቀሰችኝ ነበር፥ እኔ ግን አካለቴ ታሟል ብዬ አማረርኩ። ከዛ እርሷም፥ ካልሆነ እቤት ሆኜ እንድጸልይ ሀሳብ አቀረበች። ከዛ እግዚአብሔር ለይቶ ቤተ ክርስቲያን ሂጄ እንድጸልይ እንዳዘዘኝ አስታወስኳት። ስለዚህ ልብሴን እንድለብስ አገዘችኝና ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዛኝ ሄደች።

የዛን ጠዋት፥ ብዙ ሰው በቤተ ክርስቲያን እየጸለየ ነበረ እናም ሰውነቴ ስለታመመ እንዲጸለይልኝ ጠየቅሁ። ለመጸለይ በጣም አቅም እንደሌለኝ ነገርኳቸው። ስለዚህ ዘይት ቀብተው ስለሰውነቴ ጸለዩልኝና ከእግዚአብሔር ዘንድ መለኮታዊ ፈውስን አገኘሁ!! ሃሌ ሉያ! መጸለይና ከላይ ወደታች እየተመላለስኩ እግዚአብሔርን ስለቺሊ ህዝብ፣ ስለቤተሰቦች፣ በሱስ ስለተያዙ ሰዎችና ስለቤተ ክርስቲያን ምህረት መለመን ጀመርኹ።

ማማለዱን ጨርሼ በኋላ ላይ የዛን እለት ምሽት ጉባኤ ለመካፈል መጣሁ። ካህኑ ከባረከ በኋላ እጄን ወደ ላይ አነሳሁ እናም የሆነ ሰው ሲያልፍና ጀርባዬን ሲነካኝ ተሰማኝ። ይህ ሲሆን፥ ሙሉ በሙሉ ጥንካሬዬን አጣሁና መሬት ላይ ወደቅሁኝ። ካህኑ ምን እንደሆንኩ ጠየቀኝና ምን እንደሆንኩ አንደማላውቅ፣ አቅም እንዳጣሁና የምናገረውም የግዴን እንደሆነ መለስኩለት። ከዛ ምእመናኑ ከበውኝ በልሳን መጸለይና መጮህ ጀመሩ። ከተሰበሰቡት አንዳንዶቹ እየመጣ ከሰውነቴ እንድወጣ የሚነግረኝን መልአክ ያዩ ነበር። ካህኑ "*ሰውነትህን ለቀህ አትወጣም!*" ብሎ አዘዘ። እርሱ ይህን እንዳለ መልአኩ ከሰውነቴ እንድወጣ መጠቆሙን አቆመ። አያችሁ፥ ማንም በኢየሱስ ስልጣን ያለው ሰው በጌታ መልአክ ይከበራል።

ከዚያም ካህኑ ጠየቀኝ "*ለምን ያህል ጊዜ ነው መልአኩ ከሰውነትህ ሊወስድህ የሚፈልገው?*" ከዛ እኔ ደግሞ መልአኩን ጠየቅሁት "*ለምን ያህል ጊዜ ነው ምትወስደኝ ለአንድ ሠዓት? ለሁለት፥ ለሦስት ሠዓታት?*" መልአኩም መለሰ "*በሦስተኛው ሰማይ ኢየሱስን ለመገናኘት ለ8 ሠዓታት ትቆያለህ ምክንያቱም ሊያይህ ይፈልጋል።*" ቀጥሎም መልአኩ እንዲህ አለኝ "*አጅቤ የምወስድህ እኔ አይደለሁም ምክንያቱም እኔ በዚህች ምድር በኖርክባት በእያንዳንዷ እለት ስጠብቅህ የነበርኩት ያንተ ጠባቂ መለአክ ነኝ። ሁለት መላእክት እኩለ ሌሊት ላይ ከሰማይ ይመጡና ወደ ሦስተኛው ሰማይ ይዘውህ ይሄዳሉ።*" ይህንን ለካህኑ ነገርኩትና በሌላ ወንድም መኪና ሁለተኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኝ የፓስተር ቤት ሊወስደኝ ወሰነ። በአልጋ ላይ ጋደም እንዳልኩ ውሾች ሲጮሁና ሰዎች ሲንጫጩ ይሰማን ነበር።

ከዚህ ገጠመኝ በኋላ፥ ሁለት የሚያንጸበርቅ ደማቅ ነጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች መንገዱ መሀል ተገናኝተውን እስከ አንደኛው ፎቅ ድረስ ወጥተው ከዛ እኔ ወዳረፍኩበት ሁለተኛው ፎቅ ድረስ አብረውን እንደመጡ ተነገረኝ። እነዚህ መላእክት በጣም ያምሩ ነበር። ከበረዶ የሚነጣ አንጸባራቂ ነጭ ጸጉር፥ ልክ እንደ ፊርጥ ያጌጠ ዓይን ነበራቸው። ሰውነታቸው እንደ ህጻን ገላ ለስላሳ ሆኖ ነገር ግን ልክ እንደ የሰውነት ግንባታ እስፖርተኛ ጡንቸኛ ነው። መላእክቱ ኃያላን ናቸው!! ከዛም ለካህኑ፥ እነዚያ ወደ ገነት ሊወስዱኝ የተላኩት መላእክት እንደመጡ ነገርሁት። አንደኛው መልአክ ከሰውነቴ እንድወጣ ይጠቁመኝ ጀመር። ልክ ይህ ሲሆን

አጥንቶቼ እንደገና ማመም ጀመሩ። ስለዚህ አብረውኝ ያሉት በክርስቶስ ወንድሞቼ ሰውነቴን ማሻሸት እንዲሁም እንደ በረዶ እየቀዘቀዘ እንደሆነ ይነግሩኝ ጀመር። ቀጥሎ ሰውነቴን መልሶ ለማሞቅ ተንቀሳቃሽ ማሞቂያ ለማምጣት ሄዱ። መላእክቱ እየጠሩኝ ሳለ ግራ በመጋባት ወደዚህና ወደዚያ ጎን መገላበጥ ጀመርኩ። ሞት ሰውነቴን ሲቆጣጠረው ተሰማኝ እናም በክርስቶስ ወንድሞቼ ለሆኑት እንዲህ እያልኩ መጮህ ጀመርኹ “*እንዳትቀብሩኝ፥እመለሳለሁ!*”

ሰውነቴን ለቀቅሁ፥ እናም ከዛ አልጋዬ ላይ ዘለልኩ። በክርስቶስ ወንድሞቼ ሰውነቴን እየነኩ እንደዚህ ሲሉ አየኋቸው “*ሄደል፥ሰውነቱን ለቋል!*” ነገር ግን እኔ እዚያው አጠገባቸው ሆኜ “*እዚሁ ነኝ!*” እያልኳቸው ነበር። ሆኖም ሰውነቴ የማይበሰብስ የመንፈስ ሰውነት ስለነበረ እነርሱ አያዩኝም። ወንድሞቼ ሰውነቴን በብርድልብስ መጠቅለል ጀመሩ።

አንደኛውም መልአክ እንዲህ አለኝ “*መሄጃችን ሠዓት ነው፥ምክንያቱም ጌታ እየጠበቀህ ነው!*” እያንዳንዱም መላእክት እጅና እጄን ይዘውኝ ወደ ገነት አነሱኝ እናም በብርሃን ፍጥነት በህዋው ውስጥ አለፍኩ። ይህን እነግራችኋለሁ፥ ከነዚህ አንዳች እንኳ ባታምኑኝ፥ የእኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ህያው ነው እናም ለዘላለምም ይኖራል!!

በኋላ ላይ ጌታ ወደ ሰውነቴ እንድመለስ ሲነግረኝ፥ እንዲህ አልኩት “*አሁን ማን ያምነኛል፥ ካንተ ጋር ልሁን!! ይህን ራዕይ ማን ያምናል፥ ማንም ይህን አያምንም ምክንያቱም እምነት የላቸውም! በምድር ላይ ያለው እምነት ማነስ ግዙፍ ነው፥ ማን ይህን ገጠመኝ ያምናል?*” ጌታም መለሰልኝ “***የሆነ ሰው ያንተን ታሪክ ያምናል፥ከእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያኔ የሆኑት ብቻ ያምኑሀል።***”

የዛን ምሽት ሰውነቴን እንደለቀቅሁ፥ ጌታን ለመጎብኘት በሚገርም ፍጥነት እየበረርኩ ነበር። ምድርን ወደታች ማየት እችል ነበር። ከዛ በጨረቃ አጠገብ አለፍኩ፥ የምድሩን ምሽት የምታፈካው ደማቋ ጨረቃ። ከዛም፥ ግዙፏን ፀሐይ በዓይኔ በብረቱ ማየት ችያለሁ፤ ከፀሐይ ፈንጥቆ ምድርን የሚያሞቃትን እቶን ማየት ችያለሁ። ከዛም ስንቀጥል ብዙ ከዋክብትን በአጠገባቸው ስናልፍ ለማየት ችዬ ነበር። እግዚአብሔር ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን እንዳይ ያደረገው ለአላማ ነው፤ ያም አላማ አምላካችን ዓለሙን ሁሉ የፈጠረ ግዙፍ ፈጣሪ!! እንደሆነ ለእናንተ ለመናገር ነው። በማንኛውም መንገድ እርሱ ትንሽ አይደለም!

ፈጽሞ ምንም ዓይነት ኮከብ የሌለበት ቦታ እስክንደርስ ድረስ በሚያስገርም ፍጥነት መጓዝ ቀጠልን። ምንም ፍጥረት የለም፥ ጨለማ ብቻ። ዝቅ ስል ከታች ሁሉም ከዋክብት ይታዩኛል። መፍራትና መላእክቱን መጠየቅ ጀመርኩ “*ወዴት ነው የምትወስዱኝ? እባካችሁ ወደ ምድር ወደ ሰውነቴ መልሱኝ!*” ከዛ ጭምቅ አደረጉኝ እና አንድ አንድ እግራቸውን ከእኔ እግር ጋር አቆላለፈው ያዙኝ። ከፍርሀቴ የተነሳ በእናቴ ማህጸን እንዳለ ጽንስ (ሽል) ጉብጥ ማለት ጀመርኩ። መላእክቱም “*ዝም በል! በሦስተኛው ሰማይ ሊያናግርህ ወደሚጠብቅህ ወደ ኢየሱስ ይዘንህ እየሄድን ነው!*” አሉኝ። መላእክቱ ቆም አሉ፥ በዚህ አፍታ ዙሪያዬን ተመለከትሁ፥ ምንም ፍጥረት አይታየኝም፥የት እንዳለሁ አላውቅም ግን በሁለተኛው ሰማይ ያለሁ ይመስለኛል።

መላእክቱ ይዘውኝ ሳለ እራሴን እንደ ሽል ዓይነት ቁልፍ እያደረግሁ ነበር እናም ድንገት አሰቃቂ የግር ግር ድምጽ ከበላዬ ሰማሁ። ከዛ መላእክቱ ጭምቅ አደረጉኝና እንዲህ አሉኝ “*ሪካርዶ፥አትፍራ፥ኢየሱስ ከእኛ ጋር ነው!*” እየተናገሩ እያለ እንዲህ አሉኝ “*ቀና በልና ወደ ላይ ተመልከት!*” ከዛም በማየው ነገር በጣም ተገረምኩ ምክንያቱም የሆኑ ነገሮች ከላያችን ሲንቀሳቀሱ ይታዩኝ ነበር። እናም አንዱ መልአክ በዛ ያለውን ለማየት እጁን አወናጨፈና ከላያችን የነበረውን ሰማይ ሙሉ በሙሉ ገለጠው። ሰማዩ በተገለጠ ጊዜ ሰማዩን ከሞሉት ሰይጣናትና አጋንንት በቀር ሌላ ምንም የለም። በኢየሱስ ስም ጌታ ይገስጻቸው!! መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው! በዚህም ምድር የምታዩት እያንዳንዱ ነገር በራዕየ ዮሐንስ ላይ የምታዩት ነው። ኢየሱስ

እየመጣ ነው፥ እንዴት አድርጌ ላሳምናችሁ፥ በጣም ቅርብ ነው!! መላእክቱን "*ይሄ ቦታ ምድር ነው?*" ብዬ ጠየኳቸው። አንድኛውም እንዲህ ሲል መለሰልኝ "*ይህ ሰይጣንና ሠራዊቶቹ የሚኖሩበት ሰማያዊ የጨለማ ስፍራ ነው።*" ከዛ እንዲህ ማለት ጀመርኩ "*ለዚህ ነው በምድር ላይ ይሄ ሁሉ ክፋት ያለው! እነዚህ አጋንንት ከዚህ ስፍራ እየመጡ ነው በሰው ዘር ላይ ብዙ ኃጢአትና ጥፋት የሚሠሩት። ምድር በሰይጣናት ተሞልታለች!*" ሚሊዮኖች ጊዜ ሚሊዮኖች የማይቆጠሩ ናቸው።

ከዛም አንደኛው መልአክ በትኩረት እንዳይ ይጠቁመኝ ጀመር እናም የእነዚህን ፍጥረታት ፊት ያሳዩኝ ጀመር፥ አብዛኞቹን እነዚህን አካላት በቴሌቪዥን መስኮቶች እንድናያቸው ተደርገናል። እነዚህ አካላት ጭራቆች ናቸው! ተንደር-ካትስ እና ፓወር-ሬንጀርስ (ካርቶን ፊልም ላይ ያሉ ገጸ-ባህሪያት ስሞች ናቸው።) እናም በእውነተኛ ህይወት ካርቶን ፊልም ላይና ሆረር ፊልም ላይ የምናያቸውን ገጾች አየሁ።




እነዚህን ፊልሞችና አኒሜሽኖች የሚደርሱ ሰዎች እነዚህን ነገሮች ለቴሌቪዥንና ለሲኒማዎች ለመሥራት ከሰይጣን ጋር ስምምነት አላቸው!! እነዚህ ሁሉ ስዕሎች በዛ ቦታ ካየኋቸው መናፍስታዊ ነገሮች የመጡ ናቸው። ለምን ይመስላችኋል የዚህ ዘመን ልጆች አመጸኞች የሆኑት?? ምክንያቱ እንዚህን ፊልሞች ሲያዩ ወደ ውስጣቸው




ስለሚገቡና ስለሚቀረጹባቸው ነው። ለዚህ ነው ልጆቻችን በቴሌቪዥን ምን ማየት እንዳለባቸው መለየት እንዲችሉ መምከር ያለብን። መላእክቱ ይህ ሁሉ ህልም እንዳልሆነና እውነት እንደሆነ ነገሩኝ። እነዚህ ሁሉ ሰይጣናት አሉ፥ እናም ሰዎች እነዚህን ሰይጣናት ወደ ምድር ለማምጣት ከእነርሱ ጋር ስምምነት ያደርጋሉ። እነዚህ ሰይጣኖች እኔን፣ ቤተ ክርስቲያንን፣ አብን፣ ጌታ ኢየሱስን ምድርን መራገም ጀመሩ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር እንዲሁም ለማንኛውም ፍጥረታቱ ክብር ስለሌላቸው ነው።

ከዛ ሁጎ የተባለውን ጭራቅ በሥጋ አየሁት፥ በቺሊ ውስጥ ታዋቂ የካርቶን ገጸ-ባህሪ ነው። ለማየት አስፈሪ ነበር። ከዛ ወደ እኔ መጥቶ እንዲህ አለኝ "*ወደ ምድር ሂደን ህጻናቱን ሁሉ እንገድላቸዋለን!*" ለምን ይመስላችኋል ህጻናት ህጻናትን የሚገድሉት? ምክንያቱ አንዳንዶቹ እንዳሉት፥ የሆነ ነገር ከቴሌቪዥኑ ወጥቶ ይህንና ያን እነዲያደርጉ ስለነገራቸው ነው። ሰይጣኖቹ ምድር ላይ ጥላቻን እየተከሉ ነው፥ ጌታ ቺሊን ነፃ ያውጣት ይቀድሳት!! አንዱም መልአክ "*መመልከትህን ቀጥል*" አለኝ። እናም ሰይጣኖቹ እንዲህ አሉ "*ቤተ ክርስቲያንን ልናጠፋ ሞክርን ግን አልቻልንም ምክንያቱም አንዱን ስንገል፥ ያንን ሞት ለመተካት ሌሎች በሺህ ይነሳሉ!*" ቤተ ክርስቲያን ከተጀመረች ጀምሮ ሰይጣን ሊያጠፋት ሞክሮ ነበር፥ እውነተኛውን ወንጌል የምትሰብከውና የእግዚአብሔርን ሥራ የምትሠራውን፥ ነገር ግን አይችልም ምክንያቱም ጌታ ስለሚጠብቀን ነው! ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን! ከዛም አጋንንቱ እንዲህ አሉ "*እስቲ አዲስ ነገር እናድርግ፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንግባ፥ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእኛ የሆኑ ብዙ አሉ! እነዚህን ሰዎች ሀሜትን ለማስፋፋትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ በወንድሞች መካከል መከፋፈል ለመፍጥር እንጠቀምባቸዋለን። አብያተ ክርስቲያናትን በሀሜት እንዲወድቁ እናደርጋቸዋለን እናም መንፈስ ቅዱስ*

*ተጸይፎ ቤተ ክርስቲያኗን ጥሎ ይሄዳል።* ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን ቅን ፍርድ የሚወዱትን ለማጥፋት በየስፍራው ይሄዳል። ልክ የዚህ ጥቅስ ቃል እንደሚለው።


1ኛ ጴጥሮስ 5፡8

*በመጠን ኑሩ፥ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤*

ከዚህ በኋላ ምንም ማየት አልፈለግሁም፥ ነገር ግን መልአኩ እየሆኑ ያሉትን ነገሮች ማየቴን እንድቀጥል ነገረኝ። አንዲት የምታንጸባርቅ ደማቅ ኮከብ ስትመጣ ሰይጣኖቹ ሁሉ በየቦታው ሲበታተኑ አየሁ። ይህ ኮከብ በቀረበ ጊዜ ለጌታ ክብርና ምስጋናን ይዞ ነበር። ይህ ኮከብ ኮከብ አልነበረም፥ ሚሊየኖች መላእክት በነጫጭ ፈረሶች ላይ፥ የሠራዊት ጌታን እያመሰገኑ!! እንዲህ እያሉ ይጮኹ ነበር "*ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ከዘመናት እስከ ዘመናት የሚኖር! ጌታ አልፋና ኦሜጋ ነው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው፥ እስትንፋስ ያለው ሁሉ ጌታን ያመስግን!*" ከዛም ታላቅ ጦርነትን አየሁ፥ ሰይጣኖቹን ከዛ በኋላ ላያቸው አልቻልኩም። "*ከአሁን በኋላ አትፍራ፥ በጠላት ወገን ካለው በእኛ ወገን ያሉት መላእክት ይበልጣሉ!*"

መላእክቱ ወደ ሦስተኛው ሰማይ መንገድ ከፈቱልን። አንዱ ወደ ግራ አንዱ ወደ ቀኝ ሆነው ለሁለት ተከፈሉ። ወደ ሦስተኛው ሰማይ ክፍት መንገድ ነበረ! ይህ መንገድ እስከ ገነት ድረስ ይደርሳል እናም ሰማያዊውን የእግዚአብሔር ከተማ ማየት ትችላላችሁ።(በምድር ላይ የዚህችን ከተማ ፎቶ ያነሳ ሳተላይት አለ፥ ይህ ሰማያዊ ከተማ እውነት ነው!! በሬዲዮና በቴሌቪዥን ተላልፏል።) በእነዚህ መላእክት የተሠራውን አስደናቂና ግሩም መንገድ ለማየት ቻልኩ። መላ አካባቢውን ከሰይጣኖች ነፃ አደረጉት፥ እግዚአብሔርን ማክበርና ስሙን ማመስገን አላቋረጡም!! መላእክቱ ከፊታቸው አደረጉኝና እንዲህ አሉኝ "*እዚህ መጠበቅ ይኖርብሀል!*"

ከዚያም በሩቅ ይታየኛል፥ ከሰማያዊቷ ከተማ ነጭ እጀጠባብ የለበሰ ሰው በነጭ ፈረስ ሲመጣ አየሁ። ይህ ሰው ወደ እኔ በቀረበ ቁጥር መላእክቱ እግዚአብሔርን ማመስገንና ስሙን ማወደስ አላቋረጡም። ይህ ሰው ወደ እኔ 4 ሜትር እርቀት ድረስ መጣ። ይህ በጣም ውብ ነው፥ ከሌሎቹ መላእክት ሁሉ ይልቅ ውብ። እንዲናገረኝ እየጠበቅሁት ነበር፥ እርሱ ግን ለጥቂት ጊዜ በትኩረት ተመለከተኝ እናም ጮክ ብሎ እንዲህ አለኝ "*እኔ ነኝ! እኔ ነኝ አንተንና በምድር ያለችውን ቤተ ክርስቲያን የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠኝ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል!*" ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤልን ፊት ለፊት አየሁት እናም የተዋበ ነበር! ወደ ጎን ዞር አለና ወደ ሰማያዊቷ ከተማ እንድገባ አመለከተኝ። እንዲህ አለኝ "*ግባ! ጌታ ኢየሱስ እየጠበቀህ ነው!*" በከተማዋ መንገድ እየሄድኩ ነበር እናም እኔ እየሄድኩ መላእክቱ መጮህና እግዚአብሔርን ማመስገናቸውን አላቋረጡም። ከተማዋን እያየሁ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ።




ከተማይቱ የተሰራችው በንጹህ ብርሃን አስተላላፊ ወርቅ ነው፥ የመግቢያውም በሮች ባለ ፈርጥ ናቸው። መሬቱ ኩልል ያለ (ጥርት ያለ) ነው። እንዲህ ዓይነት ነገር በምድር ላይ ፈጽሞ አላየሁም፥ የሰው ልጅም ሊሠራው አይችልም። መሀንዲሱ (አርክቴክቱ) የእኛ ጌታና የዓለማት ሁሉ አምላክ ነው። ከከተማዋ ውጭ ነበርኩ እናም የመግቢያው በር ወለል ብሎ ተከፍቷል። እናም እነዚህ በሮች እስካሁን ክፍት ናቸው። ወደ ውስጥ ይታየኝ ነበር እና ግድግዳዎቹ ላይ ቀያይና ሰማያዊ እንቁዎች አንዲሁም የሚያንጸባርቁ ፈርጦች ነበሩበት። ከከተማዋ ውስጥ ሚሊየኖችና ሚሊየኖች ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ይሰማል! ከከተማዋ ውጭ ሆኜ ይን እየሰማው ተርተበትኹ። ገነትን ያናወጸ አንድ ድምጽ ሰማሁ እናም ከዚህ ድምጽ በኋላ ሚሊየኖችና ሚሊየኖች ድምጾች እግዚአብሔርን እንዲህ እያሉ ያመሰግኑታል

*"ቅዱስ÷ ቅዱስ÷ ቅዱስ÷ የእግዚአብሔር በግ እና አባቱ ክብርና ምስጋና ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ይገባል አሜን!"* ይህም ታላቅ ድምጽ ጮኸ "***እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ! ቅዱሳን ብቻ ወደዚህ ቦታ ይገባሉ! ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ሊያየው አይችልም!***" ያለ ቅድስና ማንም አያየውም።

የሆነ ድምጽ "*ግባ*" አለኝ ከዛም ወደ ከተማዋ ገባሁ። ከዛም በእሳት የሚንሳፈፍ የሚገርም ዙፋን አየሁ። እሳት ከዙፋኑ ሲወጣ አትኩሬ ስመለከት ኢየሱስን አየሁት÷ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ! ተልፈስፍሼ መሬት ላይ ወደቅሁ÷ ምንም አቅም አልነበረኝም። ከእሳቱ ውስጥ እጁን ወደ እኔ ዘረጋና "***ተነስተህ ቁም!***" አለኝ። ብርታት አገኘሁና ቆምሁ። ወዲያውኑ እጁን፣ እግሩንና ሰውነቱን መነካካት ጀመርኩ። ፊቱን ባየሁት ጊዜ አቋሙ÷ በምድር ላይ የጥበብ ባለሙያዎች በስዕላቸው ከሚገልጹት ጋር በፍጹም አይመሳሰልም! ብዙ ሰዎች የእንጨት አማልክትና ብዙ ምስሎችን ይሠራሉ! ግን ወንድሞቼ ልነግራችሁ የምፈልገው÷ ኢየሱስ እነዚያን ስዕሎች አይመስልም። በጣም ፈርጣማ አምላክ ነበር! መካከለኛም አልነበረም÷ ፍጹም ኃያል አምላክ ነበር!! እነዲህ አለኝ "***እኔ በእንጨትም ሆነ በቾክ(ጠመኔ) የምሠራ አምላክ አይደለሁም! እኔ እውነተኛ ህያው አምላክ ነኝ!***" ቀጥሎም "***በምድር ላለችው ቤተ ክርስቲያኔ እወነተኛ እንደሆንኩ ንገራቸው!! የእውነት አለሁ ህያውም ነኝ! ለህዝቦቼ ገነት እውነተኛ እንደሆነችና እየጠበቅኳቸው እነደሆነ ንገራቸው!***"

እነዲህ አለኝ "***ከእኔ ጋር ና እና አንድ ታላቅ ነገር አሳይሀለሁ።***" ከቆምንበት ወደ ታች ስንመለከት ምድርንና በምድር ላይ የተሠራው ሁሉ ይታየናል። ጌታም አለኝ "***ቤተ ክርስቲያኔ የምትሠራውን ሁሉ ማየት እችላለሁ!***" እኛ የምናደርገውን ሁሉ ያያል እናም አብዛኞቻችሁን ከገነት ሆኜ አየኋችሁ። ኢየሱስም "***ቤተ ክርስቲያኔን እያት!***" አለኝ። ከዛም ወንድሞችን በወንድሞች ላይ አንድ ቤተ ክርስቲያን በሌላ ቤተ ክርስቲያን ላይ አየሁ። ከዚያም ኢየሱስ ይህን ነገረኝ "***ቤተ ክርስቲያኔ እምነቷን አጥታለች! በእኔ ማመን አይፈልጉም÷ በምድር ላይ ስንፍና ተራብቷል እናም እኔ ስለመኖሬ ማመን አይፈልጉም። ለህዝቤ በምድር ላይ ታላቅ ነገር ላደርግ እንደሆነ ንገራቸው! ቤተ ክርስቲያኔ በማደግ ፋንታ ወደ ኋላ እየተንሸራተተች ነው።***" ጌታም ስለቤተ ክርስቲያኑ ማልቀስ ጀመረ÷ ለእኔም እንዲህ አለኝ "***ይህች ቤተ ክርስቲያን የእኔ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም!***" እኔም *"ጌታ ሆይ÷ እንደዚህ አትበል! እኛም ያንተ ቤተ ክርስቲያን ነን።"* አልሁት። ከዛም ጌታ መለሰልኝ "***አይደለም÷ የእኔ ቤተ ክርስቲያን በተአምራዊ ኃይል በምልክቶችና በድንቆች ነው የምትራመደው! ቤተ ክርስቲያኔ ቀንሳለች! ሆኖም ግን ንገራቸው ድጋሚ ላነሳቸው ተመልሼ እመጣለሁ!***"



አብሬው መጓዝ እንድቀጥል ነገረኝ ከዛም በሆነ በር ውስጥ አለፍን÷ መሬቱ ንጹህ ወርቅ ነበር። በወርቁ መንገድ ላይ ወደ ላይና ወደ ታች መሮጥ የወርቅ ቡናኖችን እያነሳሁ በላዬ ላይ መነስነስ ጀመርኩ። ከዛም ጌታ ተመልሼ መጥቼ በገነት የወርቅ ጎዳናዎች እንዳሉ እንድነግራችሁ ነገረኝ። "***ይሄ ሁሉ ለህዜቤ ነው።***" አለኝ ጌታ። "***ነገር ግን በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ አስራቴንና ምጽዋቴን የሚሰርቁ ብዙ ሌቦች አሉ! ለህዝቤ ማንም ሌባ በገነት መንግሥቴ እንደማይገባ ንገራቸው!***" ለጌታ ህይወታችንን ልናቃና ይገባል። ከዛ ለሚሊየኖች ሰዎች የሚሆን ብዙ ምግብና እርካታ የተሞላ ጠረጴዛ አየን። ብዙ አክሊሎችና ሰዎች እንዲጠጡባቸው÷ ጥርት ያሉ ዋንጫዎችም ነበሩ። ጌታም እንዲህ አለኝ "***ሪካርዶ÷ ይህ ሁሉ ለሁሉም ለህዝቤ እየተዘጋጀ ነበር!***" ይህ ለበጉ ሠርግ የተዘጋጀ ጠረጴዛ ነበር።

እንደኔ ወደ ገነት የሄደች በክርስቶስ አንድ እህት ነበረች እና እርሷም መላእክት ወደ ኋላና ወደ ፊት እየተመላለሱ የበጉን ሠርግ ሲያዘጋጁ አይታለች! ለጌታ እንዲህ አልኩት *"ለምንድን ነው ይህች እህት እዚህ መላእክት እያዘጋጁ ያየችው? እኔ ግን ምንም ዝግጅት ሲደረግ አላይም።"* ጌታም መለሰልኝ "***ምክንያቱም***

*ዝግጅቱ ሁሉ አልቋል!*" ለሚሠሩና ለጌታ ታዛዥ ለሆኑ አክሊሎች አሉ። ከዚያም እንዲህ አልኩኝ "*ጌታ ሆይ÷ ዝግጅቱ ሁሉ ካለቀ ታዲያ መቼ ነው የምትመጣው? እስክትመለስ ድረስ ምን ያህል ጊዜ ነው? ሠዓቱን አሳየኝ÷ በገነት አቆጣጠር ሠዓቱ ስንት ሆኗል?*" ብዙ ሰዎች በህልማቸው ሠዓቱን አይተዋል÷ ጌታ የሚመለስበት እኩለ ለሊት አካባቢ ያመለክታል። ጌታንም ጠየቅሁት "*ጌታ ሆይ እኩለ ሌሊት ሊሆን ምን ያህል ይቀራል? አንድ ደቂቃ ነው? አምስት ደቂቃ?*" ጌታም ለአፍታ ያህል ፊቴን ሲያጠና ቆይቶ መለሰለኝ "***ሪካርዶ÷ በገነት ምንም ሠዓት አልቀረም!***" እኔም መልሼ "*ታዲያ ጌታ ሆይ÷ ምንም ሠዓት ካልቀረ ለምን አልተመለስህም?*" ጌታም እጁን አነሳና በአውራ ጣቱና በጠቋሚ ጣቱ የሆነ በጣም ትንሽ ነገርን እያመለከተ እንዲህ አለ "***የቀረው ሠዓት አብ በጸጋው÷ ወደ ኋላቸው ለተንሸራቱት እንዲመለሱና የመጀመሪያ ሥራቸውን እንዲሠሩ እድል ሊሰጣቸው ነው።***" የሠራዊት ጌታ ያልተመለሰው ለእኛ ለሁላችን ጥቂት የንስሐ ጊዜ ሰጥቶን ነው÷ ያች ጥቂት ጊዜ "የአብ የጸጋው ሠዓት ትባላለች።" በማንኛውም ቅጽበት ኢየሱስ እየመጣ ነው÷ በሙሉ ልባችን ልንፈልገው፣ ልንጸምና ልንጸልይ የቀደመውንም የድሮ ሥራ ልንሠራ ይገባል። ልጨርስነው። ጌታም ደገመው "***ያለነው በእግዚአብሔር (በአብ) የጸጋው ሠዓት ነው!***"



ከዚያም መልአክ በቀኛችን በኩል መጣና ጮኸ "*ሠዓቱ ደረሰ!! ሠዓት አልቋል። ሁሉም ዝግጅት አልቋል! ኢየሱስ ሙሽሪቱን እየተቀበለ ነው!*" ጌታ እየመጣ ነው÷ ሁሉም በመጽሐፍ የተጻፈው ምልክት ተፈጽሟል! ፊልሞችም÷ የሆነ አደጋ እንደሚፈጠር እያሳዩ ነው። ሳይንቲስቶቹ የሆነ ትልቅ ነገር እንደሚመጣ ያውቃሉ÷ ምን እንደሆነ ግን አልተረዱትም! ነገር ግን እኛ ክርስቲያኖች ኢየሱስ በቅርቡ እንደሚመጣ እናውቃለን! መልአኩ ጮኾ እንደጨረሰ÷ ቀጥሎ ሌሎቹ ሚሊየኖች መላእክት በመጨረሻ ሙሽራይቱ ወደ ገነት እየመጣች ስለሆነ መዝለልና መደሰት ጀመሩ። "*ምንድር ነው እየሆነ ያለው?*" ብዬ መጠየቄን አላቋረጥሁም። ነገር ግን ማንም ትኩረት አልሰጠኝም÷ ሁሉም በመልካሙ ዜና እየተደሰቱ ነበር። ስለዚህ መላእክቱን ተቀላቀልኩና እኔም የኢየሱስን ስም ከፍ ከፍ ማድረግ ጀመርኩ! በዛ ቅጽበት÷ እጄን ወደ ላይ ሳነሳ የሆነ ሰው በሚደነቅ ፍጥነት ከገነት አውጥቶ ወደ ታች ይዞኝ ሲወርድ ተሰማኝ።

በአሁኗ ሠዓት÷ ሙሽራይቱ ወደ ገነት እየመጣች ስለሆነ መላእክት እየተደሰቱ ነው። ወደ ምድር መጥቼ ሁል ጊዜ የምጸልይበት የቤተ ክርስቲያኑ መድረክ ላይ ወደቅሁ። **ጊዜው አጭር ነው!!** ልታምኑኝ ካልፈለጋችሁ አትመኑኝ። ነገር ግን እርሱ እየመጣ ነው÷ ይህም ለዘላለም ነው። የእግዚአብሔር ህዝቦች በመነጠቅ (መወሰድ፣ rapture 1ኛ ተሰሎንቄ 4:17) ለማመን አይፈልጉም። እባካችሁ ንቁ÷ ስለእግዚአብሔር ብላችሁ እባካችሁ ንቁ!! (*ሪካርዶ እያለቀሰ ነው።*)

ጌታ ካጠገቤ ነበር እናም እንዲህ አለኝ "***ሪካርዶ÷ መነጠቁ አሁን ቢሆን ይህን ነበር የሚመስለው!***" ከዛ መላዋን ምድርና ውዱንና የተዋበውን መንፈስ ቅዱስ÷ ሰላምና ደስታ የሚሰጠንን ምድርን ሲለቅ አየሁ። ከዛም የሆነ ትነት ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገብቶ ሲከበኝ አየሁ እናም ጌታን ጠየቅሁት "*ይሄ ምንድን ነው?*" እርሱም "***መነጠቅ ብዬ የምጠራው ይሄንን ነው።***" አለኝ። ከዛም ሰዎች ወደ ውስጥ ለመግባት ፈልገው የቤተ ክርስቲያኑን በር ሲሰባብሩና "*ልጆቼ የታሉ? ሁሉም ጠፍተዋል!*" እያሉ ሲጮኹ አየሁ። ሁሉም ምድር ላይ ያሉት ልጆች ሄደዋል ምክንያቱም እግዚአብሔር ማንንም ልጅ በኋላ ስለማይተው። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እየጮኸ መጀመሪያ የገባው የዘማሪዎች ኃላፊ ነበር÷ እየጮኸ "*ምእመናኑ የታሉ? ከኋላ ቀረሁ! እዚህ ቀረሁ! ቀረሁ!*" ከዘማሪዎች ኃላፊ በኋላ ሌሎች ፓስተሮች (ካህናት)፣ ወንድሞችና እህቶች እና የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሁሉም እያለቀሱ ነበር "*ከኋላ ቀረሁ*" ብዙ ቤተሰቦችና የትዳር አጋሮች ወዳጆቻቸውን እየፈለጉ÷

እናም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ሰዎች እንዲህ አሏቸው "*ወዳጆቻችሁ እዚህ የሉም! ጌታ ወስዷቸዋል።*" እነርሱም እያለቀሱ እንዲህ ይላሉ "*ስለዚህ ሁሉም እውነት ነበር፥ ኢየሱስ የራሱን ሙሽራ ወሰደ!*"

ሰዎች ሁሉ እያለቀሱና እዬዬ እያሉ ክርስቶስ በሆነው በኢየሱስ ባመንኩ ኖሮ እያሉ ይሙኙ ነበር። ኢየሱስ መሲሁ (ክርስቶስ) እንደሆነ የማያምን ሁሉም ጠፍቷል! ብዙ ሰዎች እና ፓስተሮች (ካህናት) ሲያለቅሱ አየሁ፥ ሰዎቹ ከፓስተሩ መልስ በመሻት "***እውነቱን ያላስተማርከው ለምንድር ነው፥ ስለጽድቅ ያላስተማርከኝና ስለዚህ ሁሉ ያላስጠነቀቅኸን ለምንድር ነው? ኋላ መቅረቴ ያንተ ጥፋት ነው!***" ይሉት ነበር። ብዙ ሰዎች የቅድስና ህይወት ስለማይኖሩ ከኋላ ይቀራሉ/ይተዋሉ። እውነተኛ ቅድስናን ልንሰብክና ሰዎችን ንስሐ እንዲገቡ ልናስተምር ይገባል! ሰዎች ፓስተሮቹን (ካህናቱን) እንዴት እንደሚመቷቸውና ልብሳቸውን እንደሚቦጫጭቁ ጸጉራቸውንም እንደሚነጩት አይቻለሁ። ፓስተሮቹ (ካህናቶቹ) እያለቀሱ እንዳይጎዷቸው ሰዎቹን ይለምኑ ነበር። ሰዎቹ ግን አያቆሙም ምክንያቱም አሁን ሰይጣናዊ ሆነዋል።

ከኋላ ሁሉም ምእመናን (አማኝ) የሚቀርባቸው ቤተ ክርስቲያናት አሉ። ከሐዘኑ የተነሳ ዓይኑን ለማውጣት የሚታገል ወንድም አይቻለሁ። ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛው መልስ መሆኑን መረዳት ባለመቻላቸው ጭንቅላታቸውን ከግድግዳ ጋር ያጋጩ ነበር። ምክንያቱም ሰዎች በኃጢአትና በእርኩሰት መቀጠል ስለሚፈልጉና ህይወታቸውን እነርሱ በሚፈልጉት መልኩ መኖር ስለሚሹ ነው። ሰዎች ራሳቸውን ሲቆራርጡ ሰውነተቻው ከጭንቅላታቸው ተበጥሶ ወደ መሬት እስኪወድቅ ድረስ ራሳቸውን ሲሰቅሉ ታያላችሁ። ራሳቸውን ከሚጎዱ ሰዎች የተነሳ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደም ዝም ብሎ ሲፈስ አየሁ። ከዛም አንድ ወጣት ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አየሁ "*እባክህ ጌታ ሆይ ውሰደኝ!*" በጣም እረፍዶ ነበር፤ ኢየሱስ አንዴ መጥቶ የእርሱን ሙሽራ ወስዷል። በጣም ብዙ ዘግናኝ ነገሮችን ስላየሁ በመሬት ላይ ወደቅሁ።

ኢየሱስ እንዲህ አለኝ "***በታላቁ መከራ ጊዜ፥ ከዚህ በፊት ፈጽሞ ያልነበረ መከራ ይሆናል።***" ከዛ፥ እኔም ጠየቅሁት "*ለምንድር ነው ሰዎች ራሳቸውን ክፉኛ ከጎዱ በኋላ እንደገና ዘለው የሚነሱት?*" ጌታም መለሰልኝ "***ምክንያቱም በዚህ ሠዓት ሰዎች ሞትን ይመኛሉ ግን አያገኟትም። ሞት ከእነርሱ ይሸሻል።***" ጌታን፦ "*ለምንድር ነው እነዚህ ሁሉ ፓስተሮች (ካህናት) እና ሰዎች የቀሩት?*" ብዬ ጠየቅሁት። ጌታም እንዲህ አለ "***ምክንያቱም ስለማውቃቸው ነው። ልባቸውን አውቀዋለሁ።***" እግዚአብሔር ያውቀናል። እርሱ የሁላችንንም ልብ ያውቃል። ወደ መሬት ወደቅሁ፥ ለጥቂት እራሴን ልስት ነበር። ኢየሱስም እንደዚህ አለ "***ይህንን ላሳይህ የፈለግሁት ቤተ ክርስቲያኔን እንድታስጠነቅቅና ተስፋ እንድትሰጣቸው ነው። ሰዎች አሁን ንስሐ ቢገቡ ጊዜ እስካለ ድረስ እንደምምራቸው ንገራቸው። በምድር ላይ ታላቅ ነገርን አደርጋለሁ።***"

እባካችሁ ዓይናችሁን ክፈቱ። በቺሊ በወንጌል የሚያምኑ ቤተ ክርስቲያኖች እየበዙ ነው። "***ህዝቤ ይቅርታን ከጠየቁ እንደምቀበላቸው ንገራቸው።***" ከዛም ሌላ ራዕይ አየሁ፥ እናም እሳት ሰማይን በሙላ ሸፈኖ አየሁ። ጌታም እንዲህ አለኝ "***አየኸው? ይህ በምድር ላይ የምታየው እሳት፥ በሀገረ ቺሊ ላይ የመጣ እሳት ነው። ምክንያቱም ቺሊ የክርስቶስ ትሆናለች! እግዚአብሔር ቺሊን ይለውጣታል!***" ከዛም በቺሊ ላይ የሚመጣውን የመጀመሪያውን እንቅስቃሴ አየሁ እናም ኢየሱስ እንዲህ አለኝ "***የአባቴ ዓይኖች በቺሊ ላይ ናቸው።***" እሳቱ በቺሊ ላይ በወደቀ ጊዜ፥ ሌሎች ሀገሮች ያውቃሉ እግዚአብሔርም በቺሊ እየሠራ እንደሆነ ያስተውላሉ። በቺሊ ላይ ባለው የእግዚአብሔር ሥራ ምክንያት በመላው ዓለም ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተደሰቱ። ጌታ በራዕይ "ፓሲኦ ሁማንዳ" ("Paseo Humada") የተባለ ቦታ ወሰደኝና ቆማጣዎችና ሽባዎችን አሳየኝ። ከዛም እውነተኛ አማኞች እግር ለሌላቸው ለቆማጦች ሲጸልዩላቸውና ቅልጥማቸው እንዲያድግ ሲያዙት አየሁ። አይናቸው እያየ ቅልጥማቸው ሲታዘዝና ሲያድግ አየሁ። እጅም የሌላቸው ሰዎች ወዲያውኑ እጅ ይፈጠርላቸዋል። በዚህ ጊዜ ጌታ አዳዲስ ተአምር ያሳያል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ይፈወሳሉ። በዚህ

ቀን የሞተ ይነሳል፥እናም እግዚአብሔር የድሮዎቹ ሐዋርያት በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳደረጉት እንደዚህ ዓይነት ተአምር እንድታደርጉ በቺሊ ይጠቀምባችኋል።

ይህ እግዚአብሔር የሰጠኝ ጠቅላላ ራዕይ ነው (ሪካርዶ ሲድ)። በቅርቡ ይመጣል፥ አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና! (ማራናታ፣ Maranatha!) አሜን!




ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, matoughen@gmail.com